# በኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

## የስፔስ ቁሶችና ተግባራት ምዝገባ ፣ ኢንስፔክሽን ፣ቁጥጥርና ፈቃድ መመሪያ

**ቁጥር 573/2013**

ሐምሌ- 2012
አዲስ አበባ

ማውጫ


መግቢያ........................................................................................................ 1

ክፍል አንድ..................................................................................................... 1

ጠቅላላ ........................................................................................................... 1

1. አጭር ርእስ.................................................................................................. 1
2. ትርጓሜ......................................................................................................... 1
3. የመመሪያው አላማ....................................................................................... 4
4. የመመሪያው አስፈላጊነት............................................................................... 4
5. የተፈጻሚነት ወሰን........................................................................................ 4

ክፍል ሁለት.................................................................................................... 5

የኢንስቲትዩቱ ተግባር እና ሃላፊነት፣ የስፔስ ቁሶች ማሳወቅና ምዝገባ.............................. 5

6. የኢንስቲትዩቱ ተግባርና ሀላፊነት...................................................................... 5
7. መርህ............................................................................................................ 5
8. ስለማሳወቅ.................................................................................................... 6
9. የማሳወቅ ስርአት አፈጻጸም .............................................................................. 6
10. ምዝገባ ........................................................................................................ 6
11. የምዝገባ አፈጻጸም.......................................................................................... 7

ክፍል ሶስት .................................................................................................... 7

የፈቃድ አሰጣጥ መስፈርቶችና የአፈጻጸም ስርአት........................................................ 7

12. ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው የስፔስ ቁሶችና ተግባራት ................................................ 7
13. ፈቃድን ስለማስተላለፍ ..................................................................................... 8
14. የፈቃድ ጥያቄ................................................................................................. 8
15. የፈቃድ እድሳት............................................................................................... 9

16. ፈቃድ የሚታገድበት ወይም የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች........ 10

ክፍል አራት........ 10

ኢንስፔክሽንና ህግ ማስፈጸም ........ 10

17. መርህ........ 10

18. ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ........ 11

19. ኢንስፔክሽን እና ህግ ማሰፈጸም........ 11

20. የካሳ ጥያቄ........ 12

21. ውሳኔ........ 12

ክፍል አምስት ........ 13

በስፔስ መስክ የሚሰማሩ ባለፈቃዶች የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ........ 13

22. ለባለፈቃዶች የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ........ 13

23. የብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልግባቸው ጉዳዮች ........ 13

24. የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ ........ 13

ክፍል ስድስት ........ 14

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ........ 14

25. ክልከላ ........ 14

26. ተጠያቂነት ........14

27. መመሪያው ወደ ኋላ ተመልሶ ስለመስራት........ 14

28. መመሪያውን ስለማሻሻል ........ 14

29. የተፈጻሚነት ጊዜ ........ 14

እዝል 1 ........ 15

የዓለም አቀፍ ህጎችና ስምምነቶች በዚህ የስፔስ ቁሶችና ተግባራት ቁጥጥር መመሪያ አካል ተደርገው የሚወሰዱት የዓለም አቀፍ የስፔስ ህጎችና ስምምነቶች ........15

Treaties ........ 15

እዝል -3 ........ 16

# መግቢያ

ኢትዮጵያ የፈረመችውን የህዋ አጠቃቀም ሀብቱን ለሰላማዊ ግልጋሎት ለማዋል እና የእኩል ተጠቃሚነት መብት እንዲኖራቸው የሚያደርገውን የOuter Space Treaty ስምምነት አክብሮ ከዘርፉ የላቀ ጥቅም ለማስገኘት የተለያዩ ባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎን በማረጋገጥ ጎን ለጎን ከስፔስ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጋር ተያይዘው ከሚመጡ አሉታዊ ተጽእኖዎች ለመጠበቅ አስፈላጊ የሆኑ የመከላከያ እርምጃዎችን መውሰድ በማስፈለጉ፤

የስፔስ የቁጥጥር ስርዓት ለስፔስ ሥራ የሚያስፈልጉ ዕቃዎችን መመዝገብ፣ በግል ይዞታ ሥር የሚገኙ ሳተላይቶችንም ሆነ የሳተላይት መረጃዎችንና ምልክቶችን ማግኘት የሚቻልበትን ሁኔታ ጨምሮ አዘገጃጀቱንና ስርጭቱን፣ አጀማመሩንና የሚከናወነውን ሥራ መምራት ለማስቻል፤

በኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እንስቲትዩት ደንብ ቁጥር 393/2009 አንቀጽ 10 ን/አንቀጽ (10) የክትትልና የቁጥጥር ስራ እንዲያከናውን በተሰጠው ስልጣን ከዓለም አቀፋዊ ግዴታዎች ጋር በተያያዘ የስፔስ ዘርፉን ለሰላማዊ ዓላማ መጠቀምን ማረጋገጥን ጨምሮ በስፔስ ጉዳዮች ላይ የተሰማሩ ተቋማትን በመመዝገብ፣ ፈቃድ በመስጠት፣ በማደስ፣ ማሻሻያ በማድረግ እና እንዳስፈላጊነቱ ፈቃድ የሚቋረጥበትን የአሰራር ስርአት በመዘርጋት ማስተዳደር አስፈላጊ በመሆኑ፤

የስፔስ ቁጥጥር ስርዓትን አስመልክቶ በህግ እና በፖሊሲ የተቀመጡ የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎችን ስራ ላይ ለማዋል እንዲቻል የኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ይህንን የስፔስ ቁሶች ምዝገባ ኢንስፔክሽን ቁጥጥርና ፈቃድ መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

## ክፍል አንድ፤ ጠቅላላ

### አንቀጽ አንድ

### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የስፔስ ቁሶች ምዝገባ ኢንስፔክሽን ቁጥጥርና ፈቃድ መመሪያ ቁጥር 573/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል:

### አንቀጽ ሁለት

### ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የማያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፡-

1. "ስፔስ" ማለት ከመሬት ከባቢያዊ አየር ውጭ ያሉትን የተፈጥሮ አካላት በሙሉ የሚያጠቃልል ነው፤
2. “ስፔስ ዳታ” ማለት የስፔስ መሳሪያዎችን በመጠቀም ከስፔስና ከመሬት የሚገኙ መረጃዎች ነው፤
3. “ስፔስ መሳርያ’ ማለት በመሬትና በስፔስ ላይ የሚተከል የስፔስ ዳታ ለመቀበል ወይም ለማስተላለፍ ወይም ለማቀናበር የሚያገለግል መሳርያ ነው፤
4. “ሳተላይት” ማለት ከስፔስ ወደ መሬት ወይም ህዋ ላይ ያሉትን ስፔስ ቁሶችን ምልከታና መረጃ የሚያስተላልፍ ቴክኖሎጂ ነው፤
5. “ግራውንድ ስቴሽን” ማለት መሬት ላይ የተገነባ የስፔስ መረጃ መቀበያ፣ መቆጣጠሪያና ትዕዛዝ መስጫ ነው፤
6. “አስትሮኖሚ” ማለት ስለ መሰረታዊ ፊዚክስና ጥልቅ ስፔስ የሚያጠና ሳይንስ ነው፤
7. "ኤሮስፔስ" ማለት መሬትና ከመሬት ከባቢያዊ አየር ውጭ ያሉትን የተፈጥሮ አካላት በሙሉ የሚያጠቃልል ነው፤
8. "ኤሮስፔስ ሳይንስ" ማለት መሬትና ከመሬት ውጭ ያሉትን የተፈጥሮ አካላት የሚያጠና ዘርፈ ብዙ ሳይንስ ሲሆን አስትሮኖሚ ፣ አስትሮፊዚክስ ፣ ሳተላይት ቴክኖሎጂ ፣ የመሬት ምልከታ፣ ሪሞት ሴንሲንግ ቴክኖሎጂ፣ ስፔስ ጂኦዴሲ ቴክኖሎጂ፣ ስፔስ ሳይንስ፣ ኤሮናቲክስ፣ አስትሮናቲክስ፣ ስፔስ ኢንጂነሪንግ፣አትሞስፌሪክ ሳይንስና የመሳሰሉትን የሙያ መስኮች በሥሩ አካቶ ይይዛል፤

9. "ኤሮስፔስ ቴክኖሎጂ" በኤሮስፔስ ሳይንስ ተጠንተው የሰው ልጅ ለልዩ ልዩ ሥራ የሚጠቀምባቸውን ቴክኒኮችን ፣ ውጤቶችን፣መሳሪያዎችንና ዘዴዎችን ያጠቃልላል፤

10."የኤሮስፔስ ልማት" ማለት የህዋ ወይም የስፔስ አካላትን የመመርመር ፣ የማጥናትና ተግባራዊ የሚሆኑ የህዋ ቁሶችን ለመንደፍ ለማምረትና ለማምጠቅ የሚካሄዱ የምርምር ተግባርና የቴክኖሎጂ ልማት ነው፤

11."ኤሮኖቲክስ" ማለት ኤርክራፍት ዲዛይን እና ማኑፋክቸር ተግባራዊ የሚደረግበት ሳይንስ ሲሆን የኤርክራፍት ሳይንስን ፣ ክህሎትን ፣ የንድፈ ሀሳብን እና የተግባራዊነቱን ሥራ ጥናት የሚያካትት ነው፤

12."አስትሮናቲክስ" ማለት የስፔስ ክራፍትና ሌሎች መሰል መሣሪያዎችን የሚያጠና ሳይንስ፣ እንዲሁም የስፔስ ክራፍትን ዲዛይን ፣ግንባታና ኦፕሬሽን የሚያጠና ዘርፍ ነው፤

13. "ምርምር" ማለት አዲስ ነገር የመፍጠር፣የማላመድ፣ የማሻሻል፣ የዕውቀትና የቴክኖልጂ ሽግግር ለማድረግ በሳይንሳዊ ዘዴ የሚካሄድ ተግባር ነው፤

14. "የስፔስ ቁሶች" ማለት በኤሮስፔስ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ታስበው የተነደፉና የተፈበረኩ ቁሶች ማለትም የማምጠቂያ ማሽኖችን፣ቴሌስኮፖች፣ሪሞት ሴንሲንግ ቴክኖሎጂ መሳሪያዎች፣ትራንስፖንደሮች፣የሳተላይት መረጃ መቀበያ አንቴናዎች፣ስፔስ ጆኦዴሲ ቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ቦታ አመላካች መሳሪያ (GPS) እንደ ሳተላይት ፣ መንኩራኩር ፣ ሰው አልባ መንኮራኩሮች (UAV) እና የስፔስ ቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን ያካትታል፤

15."የስፔስ ተግባር" ማለት የስፔስ ቁሶችን የማምረት፣ የማሰራጨት፣የመነገድ፣ለስፔስ መሰረተ ልማት ወይም ለስፔስ ነክ ስራ የሚውሉ ንድፍ ስራዎችን ፣ቴክኖሎጂዎችን የማምረት፣የማሰራጨት፣የመነገድ ስራን ምክርና ስልጠናን ጨምሮ የተለያዩ አገልግሎቶች መስጠትን ያካትታል።

16. "የስፔስ ላይ በረራ ወይም እንቅስቃሴ" ማለት በሲቪል አቪየሽን አስተዳደር እና በመከላከያ ሚኒስቴር ከሚተዳደረው የአየር አገልግሎት ውጭ ያለ ሌላ የበረራ እንቅስቃሴ ነው ፤

17. “የሳተላይት መረጃ መቀበያ መሳሪያዎች” ማለት ማንኛውንም የሳተላይት መረጃ ወይም ዳታ በማንኛውም አይነት መንገድ የሚቀበል ወይም የሚያከማች ወይም የሚያስተላልፍ ወይም የሚተነትን የቴክኖሎጂ መሳሪያ ነው፤

18."ተቋም" ማለት በስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር፣ ማልማት እና የሰው ኃይል ስልጠና ዘርፍ እንዲሰራ ስልጣን የተሰጠው ተቋም ነው፤

19. ''ተቆጣጣሪ' ወይም "ኢንስትትዩት" ማለት የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ነው፤
20. "ባለፈቃድ" ማለት ከተቆጣጣሪው አካል በስፔስ ዘርፍ የስራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤
21. 'ካውንስል' ማለት የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ምክር ቤት ነው፤
22. "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
23. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
24. "ጾታ" አገላለጽ በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## አንቀጽ ሦስት

## የመመሪያው ዓላማ

ከስፔስ እና ከስፔስ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለማሳወቅ፣ለመደገፍ፣ ለመመዝገብ፣ ፈቃድ ለመስጠት፣ ለማደስ፣ ለመፈተሽ እና ለመቆጣጠር የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት እና በቀጣይነት ማሳደግ ነው፡፡

## አንቀጽ አራት
## የመመሪያው አስፈላጊነት

በኤሮስፔስ ቴክኖሎጂ፣ልማት እንዲሁም በስፔስ ሥራ ላይ ለመሠማራት የሚፈልጉ አካላትን በመመዝገብ፣ ፈቃድ በመስጠት፣ የስፔስ ቁሶች ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁና ዝቅተኛ መስፈርት በማሟላት አሠራራቸውን ለመቆጣጠርና አስፈላጊ ድጋፍ ለመስጠት እንዲቻል ይህንን መመሪያ ማውጣት አስፈልጓል፡፡

## አንቀጽ አምስት

## የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ከስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ጋር በተያያዘ፤

1. የስፔስ ቁሶችን፣ ለመጠቀሚያ፣ ለማስተማሪያ፣ ለጥናትና ምርምር፣ ለልማት ስራዎች ማስፈጸሚያ፣ ለማምረት፣ ከውጭ ለማስገባት እና ወደ ውጭ ለመላክ በሚጠቀሙ ግለሰቦች እና ተቋማት፤

2. በመመሪያው ከቁጥጥር ውጭ (excluded) እና በተቆጣጣሪው ውሳኔ ከቁጥጥር ነጻ (exempted) ከሆኑ የስፔስ ቁሶችና ተግባራት በስተቀር በማሳወቅ ብቻ በማይታለፉ ቀጣይ ቁጥጥር በሚያስፈልጋቸው የስፔስ ቁሶችና ተግባራት፤
3. መቀመጫቸው በኢትዮጵያ ሆኖ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገራት በኢትዮጵያ ስም የምህዋር ምዝገባ ያገኘ ሳተላይት በሚያመጥቁ ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።
4. ሆኖም በዚህ መመሪያ አባሪ ለስፔስ አገልግሎት የሚውሉ ከቁጥጥር ውጭ (excluded) በሆኑ አነስተኛ አቅም ያላቸው መሳሪያዎች እና ተግባራት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

## ክፍል ሁለት

## የኢንስቲትዩቱ ተግባር እና ሀላፊነት፣ የስፔስ ቁሶች ማሳወቅና ምዝገባ

### አንቀጽ ስድስት

### የኢንስቲቲዩቱ ተግባርና ኃላፊነት

የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ከዚህ በታች የተመለከቱት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፦

1. በዚህ መመሪያ ላይ የተጠቀሱ ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ዝቅተኛ ተፈላጊ መስፈርቶችን ያዘጋጃል።
2. ከስፔስ ጋር የሚገናኙ የቁሶችና ተግባራት ምዝገባ ያካሂዳል።
3. በዘርፉ ለሚሰማሩ አመልካቾች የብቃት ማረጋገጫ እና ፈቃድ ይሰጣል።
4. በዘርፉ የኢንስፔክሽን እና የቁጥጥር ስራ ያካሂዳል።
5. ለስራው አጋዥ የሆኑ ቴክኒካል ኮሚቴ ያቋቁማል።
6. መመሪያው ተፈጻሚ እንዲሆን አስፈላጊውን የክትትልና የቁጥጥር ስራ ይሰራል፣ እንደአስፈላጊነቱ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል።
7. በዘርፉ በሚከናወኑ ተግባራት ምክንያት ጉዳት ሲደርስ ለሚመለከታቸው የጸጥታ፣ የደህንነት እና የፍትህ አካላት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ያሳውቃል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል።

8. ከትራንስፖንደር ጋር በተገናኘ ጉዳዩ የሚመለከተው የመንግስት አካል ተገቢውን ቴክኒካዊ እርምጃ እንዲወስድ ኢንስቲትዩቱን ሲጠይቅ ኢንስቲትዩቱ ይህንን ያስፈጽማል፡፡

## አንቀጽ ሰባት

## መርህ

የማሳወቅ ተግባር በዋናነት ኢንስቲትዩቱ ከስፔስ ቁሶች ጋር በተገናኘ ተገቢውን የቁጥጥር ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ እንዲረዳው የሚያስችል መረጃዎችን አስቀድሞ ለማቅረብ ሲሆን በማሳወቅ ብቻ ለተፈለገው አላማ ሊውሉ ወይም ሊሰማሩ የሚችሉ የስፔስ ስራዎችን በመለየት ማቀላጠፍ እንዲያስችል የሚከናወን ተግባር መሆን ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ ስምንት

## ስለማሳወቅ

1. ማንኛውም የስፔስ መሳሪያ፣ቁስ ከዉጭ ማስገባት እና ማስወጣት ወይም የስፔስ ቁስ መገልገያ መሳሪያ የማምረት፣የመገጣጠም፣የመጠቀም፣ የማስተላለፍ፣ የማውረስ ወይም የመሸጥ ስራ ለማከናወን የሚፈልግ ሰው እንቅስቃሴ ከማድረጉ በፊት ለኢንስትትዩት ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የስፔስ ቁሱ ለምን አገልግሎት እንደሚውል ወይም ከዚህ በፊት ተመዝግቦ ከነበረው አድራሻ ለውጥ ለማድረግ ወይም ተግባሩን ለማቋረጥ ወይም የስፔስ ቁስ ስራ  ለመለወጥ ሲፈልግ ወይም ያወጋገድ ሁኔታውን ጨምሮ አገልግሎት ሲያበቃ ለኢንስቲትዩቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

### አንቀጽ ዘጠኝ

### የማሳወቅ ስርዓት አፈጻጸም

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 የተገለጸው የሚመለከተው ማንኛውም ሰው ወይም ተቋም በአካል ቀርቦ ወይም ተቆጣጣሪው አካል ባዘጋጀው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ድረ-ገጽን በመጠቀም የማሳወቅያ ቅጹን መሙላት እና ተያያዥ ሰነዶችን በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፡፡

## አንቀጽ አስር

## ምዝገባ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት፡-

1. በሀገር ውስጥ ለመጠቀሚያነት፣ ለማስተማሪያ፣ ለጥናትና ምርምር፣ ለልማት ስራዎች ማስፈፀሚያ ከውጭ ሀገራት ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ የስፔስ ቁሶች ፤
2. በሀገር ውስጥ ተገጣጥመው ወይም ተመርተው ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚውሉ ወይም ወደ ውጭ ሀገራት የሚላኩ የስፔስ ቁሶች፤
3. በኢትዮጵያ ስም የምህዋር ምዝገባ ተካሂዶላቸው በሌሎች ሀገራት በልጽገው የሚመጥቁ ሳተላይቶች በኢንስትዩቱ እንዲመዘገቡ ማድረግ አለበት፡፡

## አንቀጽ አሥራ አንድ

## ምዝገባ አፈጻጸም

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 የተዘረዘሩትን ስራዎች ለማከናወን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው፡-

1. ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ወይም በአገር ዉስጥ ተገጣጥመው ወይም ተሰርተው ወደ ስራ ሊገቡ የታሰቡ የስፔስ ቁሶችን አስመልክቶ በኢንስትዩቱ በተዘጋጀ የማመልከቻ ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ አለበት፤
2. አመልካቹ ከማመልከቻ ቅጹ ጋር የስፔስ ቁሱን ዝርዝር መግለጫ እና ተያያዥ ሰነድችን አያይዞ ያቀርባል፤
3. ኢንስቲቲዩቱ የቀረቡለትን ሰነዶች በዚህ መመሪያ አባሪ 4 ከተያያዘው የዝቅተኛ መስፈርቶች ጋር ያመሳክራል፤የተሟላ መሆኑን ሲያረጋግጥ ምዝገባ ያካሂዳል፤ የምዝገባ ማረጋገጫ ደብዳቤ ለሚመለከተው አካል ይጽፋል፡፡

# ክፍል ሶስት

# የፈቃድ አሰጣጥ፣ መስፈርቶችና የአፈጻጸም ስርዓት

## አንቀጽ አስራ ሁለት

## ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው የስፔስ ቁሶችና ተግባራት

የሚከተሉት የስፔስ ቁሶችና ተግባራት ከምዝገባ በተጨማሪ ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል፡-

1. ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ለተለያየ አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ የስፔስ ቁሶች እና ከሳተላይት የሚገኙ መረጃዎች እና ስርጭታቸው፤
2. ማንኛውም ሳተላይትን ወይም የሳተላይት መረጃን በመጠቀም የስርጭት ወይም የንግድ ስራ የሚሰራ ድርጅት ወይም ተቋም ለሚጠቀምበት የመሬት መረጃ መቀበያ ጣቢያና የስፔስ ቴክኖሎጂን ለመጠቀም ለሚውሉ መሳሪያዎች ፣
3. የሳተላይት መረጃን ለመጠቀም ባለቤትነቱ በኢትዮጵያ ወይም የሌላ ሀገር ሳተላይት ላይ ትራንስፖንደሮችን ለማስቀመጥ ወይም ለመከራየት፤
4. ለብሮድካስት አገልግሎት ኢንስቲትዩቱ የሚያመቻቸውን የትራንስፖንደር አገልግሎት ለመጠቀም፤
5. ማንኛውም የኢንተርኔት አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ድርጅት በባለቤትነትም ሆነ በኪራይ ለሚጠቀምበት የሳተላይት ቴክኖሎጂ፤
6. በኢትዮጵያ ስም የምህዋር ምዝገባ የተደረገላቸው በሌሎች ሀገራት ወይም በሀገር ውስጥ በልጽገው የሚመጥቁ፤
7. ከኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ውጭ ወደ ህዋ ወይም ስፔስ በኢትዮጵያ ስም የመጠቁ ማንኛውም የስፔስ ቁሶች
8. በኢትዮጵያ መንግስት ግዛት ውስጥ ሳተላይትን ለማምጠቅ የሚያስችል የማምጠቂያ ጣቢያ ለመገንባት፣
9. በሀገር ውስጥ የሚገጣጠሙ እና የሚመረቱ ለሲቪል አገልግሎት ሊውል የሚችል የስፔስ ቁሶች፤
10. በሀገር ውስጥ የሚተከሉ ወይም ተግባራዊ የሚደረጉ ለሲቪል አገልግሎት ሊውል የሚችል የሳተላይት መረጃ መቀበያ መሳሪያዎች እና የምድር መቆጣጠሪያ ጣቢያ፤
11. በሌላ አገር የሚመጥቁ የኢትዮጵያ ሳተላይቶች ሆነው የአስመንጣቂ አካላት የማምጠቂያ ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል፤ ሆኖም ከፈቃዱ በፊት በአገሮቹ መካከል የተደረገው ስምምነት ለፈቃድ ሰጪው አካል መቅረብ አለበት፡፡

## አንቀጽ አስራ ሶስት

## ፈቃድን ስለማስተላለፍ

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 በተዘረዘሩ የስፔስ አገልግሎትን ለመጠቀም፣ ለንግድ ተግባር ማዋል ወይም በየትኛውም ሁኔታ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ለማስተላለፍ በቅድሚያ ከኢንስቲትዩቱ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃድ ሰጭው ፈቃድ የሚተላለፍለት አካል ተገቢውን መስፈርት ስለማሟላቱ በቅድሚያ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

## አንቀጽ አሥራ አራት

## የፈቃድ ጥያቄ

1. ፈቃድ ጠያቂው አካል የፈቃድ ማመልከቻ ቅጹን እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶችን አያይዞ ለኢንስቲቲዩቱ ያቀርባል፤
2. ፈቃድ ሰጪው አካል የቀረበለትን ማመልከቻ እና ተያያዥ ሰነዶች የዚህ መመሪያ አባሪ የሆኑትን ዝቅተኛ መስፈርቶች እና እንደ አስፈላጊነቱ ኢትዮጵያ ፈራሚ የሆነችባቸውን ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች እና ስምምነቶች መሰረት በማድረግ የሰነድ ምርመራ ያካሂዳል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የአካል ምልከታ ያደርጋል፤
3. ኢንስቲትዩቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን የሰነድ ምርመራ እና የአካል ምልከታ ለማድረግ ተቆጣጣሪ አካል ወይም የቴክኒካል ኮሚቴ ሊመድብ ይችላል፤
4. ኢንስቲትዩቱ ባከናወነው የሰነድ ምርመራ እና የአካል ምልከታ ውጤት መሰረት ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ተጨማሪ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ሊጠይቅ ይችላል፤
5. የስፔስ ቁሱ ጉምሩክ የደረሰ ከሆነ ኢንስቲቲዩቱ የሰነድ ምርመራውን መሰረት በማድረግ እንዲገባ ወይም እንዳይገባ የሚል ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፤ ውሳኔውንም ከ 5 የስራ ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለአመልካቹ ያሳውቃል፤
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተሰጠው ውሳኔ እንዲገባ ከሆነ አመልካቹ የስፔስ ቁሱን ከጉምሩክ ለማስገባት ብቻ ፈቃድ ሰጪው አካል የማስገቢያ ፍቃድ ይሰጠዋል፤
7. ሆኖም አመልካቹ በስፔስ ቁሱ መጠቀም ወይም ወደ ሌላ አካል በሽያጭ ወይም በስጦታ ማስተላለፍ ከፈለገ ፈቃድ ጠያቂው ወይም የሚተላለፍለት ሰው ወደ ኢንስትቲዩቱ ቀርቦ የስፔስ ቁሱን ለሲቪል አገልግሎት ለመጠቀም ብቻ የሚያስችለውን መስፈርት ማሟላቱ ሲረጋገጥ የመጠቀም ፈቃድ እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል፡፡

8. ለሲቪል ፣ ለመከላከያና ደህንነት አገልግሎት (Dual Use) የሚውል የስፔስ ጉዳዮች የማስገባትም ሆነ የመጠቀም ፈቃድ ለኢንስቲትዩቱ ሲያቀርብ ከሚመለከታቸው የደህንነት እና የመከላከያ አካላት ጋር በመተባበር ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡ኢኒስቲቲዩቱ ይህንን በሚመለከት ዝርዝር የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

## አንቀጽ አስራ አምስት

## የፈቃድ እድሳት

1. ማንኛውም ባለፈቃድ የስራ ፈቃዱን በየሁለት (2) አመቱ ማሳደስ አለበት፣ፈቃዱን ለማሳደስ ከሚያቀርበው ማመልከቻ ጋር ለፈቃድ እድሳት የሚያበቃው መሆኑን ዝርዝር ሪፓርት ማቅረብ አለበት፡፡
2. ኢኒስቲቲዩቱ ፈቃዱን የሚያድሰው ባለፈቃዱ ከዚህ በፊት የተሰጠውን ፈቃድ ለታለመለት አገልግሎት እና ፈቃድ የተሰጠባቸው ሁኔታዎች የተሟሉ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡
3. የመጠቀም ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ኢኒስቲቲዩቱ ስለ ዕድሳት በአባሪ 7 ላይ በተያያዘው የእድሳት ዘመን መሰረት ማሳደስ አለበት፡፡

## አንቀጽ አስራ ስድስት

## ፈቃድ የሚታገድበት ወይም የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

ባለፈቃዱ፡-

1. በተሰጠው ፈቃድ ላይ ከተመለከተው ወሰንና ፈቃድ ከተሰጠበት ሁኔታ ውጭ ለሌላ ተግባር መዋሉን መረጃ ሲደርስ እና ተጨባጭነቱ ሲረጋገጥ፤
2. ፈቃዱን ሳያሳድስ ከስድስት ወር በላይ ካለፈውና ለጊዜው ፈቃዱ ታግዶ በሚሰጠው ተጨማሪ ስድስት ወር ጊዜ ውስጥ እድሳቱን ካልፈጸመ፤
3. በፈቃድ ሁኔታዎች ከተገለጹት መስፈርቶች አንድሎ ስለመገኘቱ በኢንስፔክሽን ምርመራ በተጨባጭ ሲረጋገጥ እና የጎደሉትን መስፈርቶች በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የማያሟላ ከሆነ ፤

4. የመጠቀም ፈቃድ የወሰደው ሀሰተኛ መረጃ ወይም ሰነድ አቅርቦ መሆኑ በተጨባጭ ሲረጋገጥ፤

5. የመጠቀም ፈቃድ የወሰደበትን ስራ በማናቸውም ምክንያት የተወ እንደሆነ፤

6. ፈቃድ የወሰደበትን ስራ መስራት እንደማይችል በፍርድ ቤት ሲወሰንበት ተሰጥቶት የነበረው ፈቃድ ይሰረዛል፡፡

## ክፍል አራት

## ኢንስፔክሽን እና ህግ ማስፈጸም

### አንቀጽ አስራ ሰባት

### መርህ

የኢንስፔክሽን ስራ የሚከናወነው

1. በስራ ላይ ጉዳት የሚደርስ ከሆነ ለመከታተልና ተገቢውን ህግ የማስፈጸም እርምጃ ለመውሰድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ጉዳት ለደረሰበት ግለሰብ፣ ተቋም ወይም አገር የመድን ሽፋን እንዲያገኝ ለማድረግ፤
2. የፈቃድ እድሳት የሚያስፈልጋቸው የስፔስ ቁሶችና ተግባራት በወቅቱ መታደሳቸውን ለማረጋገጥ እና
3. ከታቀደው አላማ ውጭ የሚከናወን እና እድሳት የሚያስፈልጋቸው የስፔስ ቁሶች እና አገልግሎት ፈቃድ ስራዎች እድሳት በወቅቱ ሳይከናወን ከቀረ እንዲሁም ያለፈቃድ በስፔስ ቁሶች እና አገልግሎት ስራ ላይ ተሰማርተው በሚገኙ ላይ በኢንስትቲዩቱ ወይም ጉዳዩ በሚመለከተው አካል ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለማድረግ ነው፡፡

### አንቀጽ አስራ ስምንት

### ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር

ኢንስቲትዩቱ፡-

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8፣9፣10፣12፣13 እንዲሁም 15 መሰረት በህጋዊ መንገድ ወደ ስራ በተሰማሩ ባለፈቃዶች ላይ ስለ ስራ አፈጻጸማቸው ወቅታዊ የሆነ ቁጥጥር ያደርጋል፤
2. በተካሄደው ክትትልና ቁጥጥር መሰረት ባለፈቃዱ የተሰጠውን እርማት ተቀብሎ ማስተካከያ ማድረጉን ወይም አለማድረጉን ለማወቅ የኢንስፔክሽን ስራ ያከናውናል፤

3. ፈቃድ እንደሚያስፈልጋቸው በኢንስቲትዩቱ የተለዩ የስፔስ ቁሶች እና ተግባራት ላይ የመጠቀም ፈቃድ ሳያወጣ ወደ ስራ የገባ ግለሰብ ወይም ተቋም እንዳይኖር ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ያካሂዳል፡፡

**አንቀጽ አስራ ዘጠኝ**

**ኢንስፔክሽን እና ህግ ማስፈጸም**

1. ኢንስቲቲዩቱ በየዓመቱ መደበኛ የኢንስፔክሽን የጊዜ ሰሌዳ አዘጋጅቶ ያሳውቃል፣ ይተገበራል፡፡
2. ኢንስፔክሽን ቁጥጥር የሚካሄደው በቅድሚያ ለባለፈቃዱ አስቀድሞ በማሳወቅ ከጠዋቱ 2፡00 እስከ ምሽቱ 12፡00 ባለው ጊዜ ውስጥ ይከናወናል፤
3. በዚህ አንቀጽ ን/አንቀጽ (1) እና (2) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ኢንስቲቲዩቱ ከማንኛውም ወገን ጥቆማ ሲደርሰው ወይም በኢንስትቲዩቱ የተለዩት ዝቅተኛ መስፈርቶች ወይም ቅድመ ሁኔታዎች ወይም ኢትዮጵያ ፈራሚ የሆነችባቸው ከቁጥጥር ስርዓቱ ጋር የተገናኙ ዓለም አቀፍ ህግጋትና ስምምነቶች ስራ ላይ እየዋሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ድንገተኛ ፍተሻ ሊያደርግ ይችላል፡፡
4. ተቆጣጣሪው ባለስልጣን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በተቋሙ ያለውን ቴክኒካል ኮሚቴ በሚያካሂደው የኢንስፔክሽን ስራዎቹ ውስጥ ማሳተፍ ይችላል፡፡
5. በኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ስራ ላይ የሚሳተፍ ማንኛውም የተቆጣጣሪው መስሪያቤት ሰራተኛ የቁጥጥር ስራ በሚያካሂድበት ወቅት በቅድሚያ የተቆጣጣሪው ባለስልጣን መስሪያቤት ባልደረባ ስለመሆኑ የሚገልጸውን መታወቂያ ካርድ እና ህጋዊ ደብዳቤ ለባለፈቃዶች ማሳየት አለበት፡፡
6. ተቆጣጣሪው አካል የኢንስፔክሽን ውጤቱን መሰረት በማድረግ ለባለፍቃዱ እንደ ጉዳዩ ክብደት ከአንድ ሳምንት እስከ ስድስት ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ማስተካከያ እንዲያደርግ እና ለተቆጣጣሪው አካል እንዲያሳውቅ በደብዳቤ ይገለጽለታል፤ ባለፈቃዱ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አስፈላጊውን ማስተካከያ አለመውሰዱ ሲረጋገጥ ተገቢው የህግ ማስፈጸም እርምጃ ይወሰዳል፡፡

**አንቀጽ ሀያ**

**የካሳ ጥያቄ**

በስፔስ ቁሶች ወይም ተግባራት ምክንያት የሚደርስ ጉዳት ተጠያቂነት እና ካሳ ኢትዮጵያ ፈራሚ የሆነችባቸው በአለም አቀፍ ህጎች መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ ሀያ አንድ

### ውሳኔ

1. ኢንስቲቲዩቱ የሰጠውን ፈቃድ በተመለከተ የሚሰጠውን ውሳኔ አስመልክቶ የኢንስቲትዩቱን ድረ-ገጽ ጨምሮ በሌሎች አማራጭ የመገኛኛ ዘዴዎች ለህብረተሰቡ ያሳውቃል፡፡
2. በዚህ መመሪያ አተገባበር ላይ ኢንስቲትዩቱ የሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው አካል ውሳኔው በደረሰው በ 15 ቀን ውስጥ ቅሬታውን በጽሁፍ ለኢንስትትዩቱ የበላይ ሀላፊ ማቅረብ አለበት፡፡
3. የበላይ ሀላፊ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻው አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል፡፡
4. በዚህ አስተዳደራዊ ውሳኔ ያልተስማማ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ተቋም ጉዳዩን ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት መውሰድ ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## በስፔስ መስክ የሚሰማሩ ባለፈቃዶች የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ

### አንቀጽ ሀያ ሁለት

### የብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች

ከስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት ጋር የተገናኘ በስፔስ ተግባር ውስጥ የሚሳተፉ ግለሰብ እና ተቋማት ኢንስቲትዩቱ ከሚመለከተው የፌደራል እና የክልል የንግድና ኢንዱስትሪ ወይም መሰል የመንግስት ተቋም ጥያቄው ሲቀርብ ተገቢውን ፍተሻ በማድረግ ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ ሀያ ሦስት

## የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ

በስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት መስክ የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጠው ጥያቄ ላቀረበ ማንኛውም ሰው ኢንስትቲዩቱ በሚከተለው አግባብ ጥያቄውን ያስተናግዳል፤

1. ከንግድና ኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮዎች ለሚቀርቡ የምርት የምስክር ወረቀት፣ የአገልግሎት የምስክረ ወረቀት ፣ የስርዓት የምስክር ወረቀት እና የሰው ኃይል የምስክር ወረቀት ማረጋገጫ ጥያቄዎች ሲቀርቡ ግምገማ ይደረጋል፤ በዚህ መመሪያ አባሪ ዝቅተኛ መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ ማረጋገጫ ይሰጠዋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የቀረበው ጥያቄ በአባሪው የተቀመጡ ዝቅተኛ መስፈርቶችን ያላሟላ ከሆነ አመልካቹ የጎደሉትን አሟልቶ እንዲቀርብ ይገለጽለታል፤ የማያሟላ ከሆነ

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ ሃያ አራት

## የመሸጋገሪያ ጊዜ

1. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኢንስቲትዩቱ የትራንስፖንደር አገልግሎት እስኪያመቻች ድረስ ለኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ለሚቀርቡ አዳዲስ የቴሌቪዥን ጣቢያ የፈቃድ ጥያቄዎችም ሆነ ነባር የፈቃድ ዕድሳት ጥያቄዎችን ለማስተናገድ እየተጠቀሙ ያለውን የትራንስፖንደር አገልግሎት አስመልክቶ ኢንስቲትዩቱ ማረጋጋጫ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ ሃያ አምስት

## ክልከላ

1. ማንኛውም ግለሰብ ወይም ተቋም የኢንሰቲቲዩቱ ፈቃድ ሳይኖር የስፔስ ቁሶችን ማምረት፣ መገጣጠም፣ መሸጥ ወይም ከውጪ ሃገር ወደ ሃገር ውስጥ ማስገባት ወይም ማስወጣት አይችልም፡፡

2. ማንኛውም ባለፈቃድ ለኢንስቲቲዩቱ ሳያሳውቅ የተሰጠውን ፈቃድ ለሌላ ለማንኛውም አካል ማስተላለፍ ክልክል ነው፡፡
3. የመጠቀም ፈቃድ ያልተሰጠው ማንኛውም ሰው በስፔስ ቁሱ መገልገል ወይም በስፔስ ተግባራት ላይ መሰማራት አይችልም፡፡

## አንቀጽ ሃያ ስድስት

## ተጠያቂነት

በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን ግዴታዎችና ክልከላዎች ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው እንደአስፈላጊነቱ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፤ በተጨማሪም በህግ እንዲጠየቅ ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ሰባት

## መመሪያው ወደ ኋላ ተመልሶ ስለመስራት

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ቀደም ብለው ወደ አገር ውስጥ የገቡ የስፔስ ቁሶች ወይም ለዚህ ዓላማ የተሰማሩ ተቋማት ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ በ 90 ቀናት ውስጥ መመዝብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ስምንት

## መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስትሩ ይህንን መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መሻር፣መለወጥ፣ወይም ማሻሻል ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ዘጠኝ

## የተፈጻሚነት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጸደቀበት .........ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አብርሃም በላይ (ዶ/ር)

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር

ሐምሌ 2012

አዲስ አበባ

## የዓለም አቀፍ ህጎችና ስምምነቶች በዚህ የስፔስ ቁሶችና ተግባራት ክትትልና ቁጥጥር መመሪያ አካል ተደርገው የሚወሰዱት የዓለም አቀፍ የስፔስ ህጎችና ስምምነቶች

**Treaties**

The treaties commonly referred to as the "five United Nations treaties on outer space" are:

1. The "Outer Space Treaty"
    - Treaty on Principles Governing the Activities of States in the Exploration and Use of Outer Space, including the Moon and Other Celestial Bodies
    - Adopted by the General Assembly in its resolution 2222 (XXI), opened for signature on 27 January 1967, entered into force on 10 October 1967
2. The "Rescue Agreement"
    a. Agreement on the Rescue of Astronauts, the Return of Astronauts and the Return of Objects Launched into Outer Space
    b. Adopted by the General Assembly in its resolution 2345 (XXII), opened for signature on 22 April 1968, entered into force on 3 December 1968
3. The "Liability Convention"
    a. Convention on International Liability for Damage Caused by Space Objects
    b. Adopted by the General Assembly in its resolution 2777 (XXVI), opened for signature on 29 March 1972, entered into force on 1 September 1972
4. The "Registration Convention"
    a. Convention on Registration of Objects Launched into Outer Space
    b. Adopted by the General Assembly in its resolution 3235 (XXIX), opened for signature on 14 January 1975, entered into force on 15 September 1976
5. The "Moon Agreement"
    a. Agreement Governing the Activities of States on the Moon and Other Celestial Bodies
    b. Adopted by the General Assembly in its resolution 34/68, opened for signature on 18 December 1979, entered into force on 11 July 1984.

እዝል-3

ቀን (Date)………

## የፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ

(Permission Application Form)

1. የአመልካች ሙሉ ስም ……………………………………………………………………
   (Full Name of Applicant)

2. የመኖሪያ አድራሻ ……………………………………………………………………
   (Residental Address)

3. ዜግነት (Nationality) ……………………………………………………………………

4. ስልክ (Phone/Mobile)………………………………………………………

5. የዕቃው አይነት/ስም (Equipment Name)…………………………………………………………

6. የዕቃው ዝርዝር መግለጫ (Equipment Specification)……………………………………………

7. ያረጋገጠው ኃላፊ ስም እና ፊርማ ……………………………………………………………………………
   (Checked By)

8. ያፀደቀው ኃላፊ ስም እና ፊርማ ……………………………………………………………………………
   (Approved By)

ማሕተም/Seal

አባሪ-3

ቀን (Date).........

## የፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ
## (Permission Application Form)

| የአመልካች ሙሉ ስም (Full Name of Applicant) | አድራሻ (Address) | ዜግነት (Nationality) | ስልክ | ኢሜል (E-mail) |
|---|---|---|---|---|
| | የመኖሪያ (Residental) | | የቢሮ ስልክ (Phone) | |
| | የስራ (Work) | | ተንቀሳቃሽ ስልክ (Mobile) | |

9. ያረጋገጠው ኃላፊ ስም እና ፊርማ
 (Checked By) ...............................................................................................

10. ያፀደቀው ኃላፊ ስም እና ፊርማ-------------------------------------------
 (Approved by)

## የማሳወቂያ ቅጽ

የማሳወቅ ስርዓትን ለማለፍ መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች፤

1. በድርጅቱ ስም የተፃፈ ማመልከቻ ደብዳቤ
2. ከባለስልጣኑ ድረ-ገፅ() በመውሰድ የሚሞሉ ማመልከቻዎች
3. የታደሰ የንግድ ፍቃድ (ከክልል 1 ዓመት ያላለፈው) ፎቶ ኮፒ
4. የሙያ ፍቃድ ፎቶ ኮፒ
5. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ፎቶ ኮፒ
6. የስፔስ ቁሱ ለምን ዓይነት አገልግሎት እደሚውል፡
7. የስፔስ ቁሱ ቴክኒካል ስፔስሲፊኬሽን (Machine Technical Specification) ፎቶ ኮፒ

   - ለአምራቹ ድርጅት የተሰጠ ISO/IEC certificate ፎቶ ኮፒ

   -የማሽኑ ብቃት ማረጋገጫ (Machine Test Report) ፎቶ ኮፒ

   -ማሽኑ የተመረተበት ጊዜ (Date of Manufacturing) የሚገልጽ ማስረጅ (10 ዓመት ያልሞላው)

   -ማሽኑ የተገዛበት የግዥ ውል ስምምነቶች ዶክመንት ፎቶ ኮፒ
8. ከውጭ የሚያስገቡ /የሚያስመጡ ከሆነ ማስጫኛ ሰነዶች (Shipping documents — commercial invoices, air way Bill/Bill of loading, certificate of origin)

<u>**ማሳሰቢያ**</u>

- የማሳወቁ ስርዓት ሳያጠናቅቁ የፍቃድ ማውጣት ሂደት መጀመር አይቻልም፡፡
- እያንዳንዱ ባለጉዳይ የስፔስ ቁስ አስመጥቶ/ገዝቶ ወደ ተግባር ከመግባቱ በፊት ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትት መስፈርቶች አሟልቶ የኢንስቲቱ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
- በሚያቀርባቸው ዶክመንቶች ጀርባው ላይ የተቋማቸው ማህተም ማድረግ ይገበዋል፡፡

አባሪ -6

# የፈቃድ ምስክር ወረቀት

የግል ማህደር Personal ID No

የማህደር /ቁ Request No

## በኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት
## Ethiopian Space Science and Technology Institute
## የስፔስ ቁሶች የፈቃድ የምስክር ወረቀት

ስም..............................የአባት ስም.....................................የአያት ስም.....................................
First Name Middle Name Last Name

ፆታ ....... ወንድ...... ሴት.....
Sex Male Female

ዜግነት/.......................................
Nationality

አድራሻ ..........................................ከተማ..................ቀበሌ..............ወረዳ................
Address City Kebele Wereda

ፈቃድ የሰጠው ሃላፊ ስም ና ፊርማ..............................
Name and Signature of Authorized

የተሰጠበት ቀን................................................
Date of issue

እድሳት/Renewal

አባሪ -7

የግል ማህደር Personal ID No

የማህደር /ቁ Request No

## የእድሳት ማመልከቻ ቅጽ
Renewal Application Form

# በኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

# Ethiopian Space Science and Technology Institute

## የስፔስ ቁሶች የእድሳት ማመልከቻ ቅጽ

Application form for the renwal of space equipment

1. የአመልካች/Applicant's

ስም..............................የአባት ስም....................................የአያት ስም.....................................

First Name Middle Name Last Name

2. ፆታ ወንድ ሴት
Sex MaleF emale ዜግነት/.......................................Nationality

3. የዕቃው መለያ ቁጥር/ .....................................................................
Equipment part number

3.1 የተሰጠበት ቀን..................................................
Date of issue

3.2 አገልግሎት የሚያበቃበት ቀን..............................
Date of expiry

3.3 የተሰጠበት ቦታ...............................................
Place of issue

3.4 የሰጠው አካል................................................
Issuing auithority

ስልክ ቁጥር ሞባል..............................የቤት ስልክ..................

<u>ለቢሮ ሥራ ብቻ/For office use only</u>

የማመልከቻ ቅፁንና አባሪ ሆነው የተያያሁትን ሰነዶች ተመልክቶ ያረጋገጠውና ውሳኔ የሰጠው

ሃላፊ ሙሉ ስም.................................................... ቀን................................

የተከፈለው ገንዘብ ልክ........................................... የደረሰኝ ቁጥር .......................

የገንዘብ ተቀባይ ሙሉ ስም....................................... ቀን .......................

የኢንስቲትዩቱ ማህተም

አባሪ-8

ቀን (Date).........

# የውሳኔ ይግባኝ ማቅረቢያ ቅጽ
# (Appeal Form)

1. የይግባኝ አቅራቢ ሙሉ ስም .....................................................
   Name of a person filing a complaint
2. የይግባኝ አቅራቢ አድራሻ .....................................................
   Address of a person filing a complaint
3. የተፈፀመው ድርጊት ወይም የቅሬታው ይዘት ምንድን ነው?
   What is your complaint all about?

   ....................................................................................

4. ቅሬታ የቀረበበት ቀን .....................................
   Date on which an event against which a complaint is filed be occurred
5. የቅሬታ እውነትነት ሊያስረዱ የሚችሉ ማስረጃዎች/ካሉ/
   Evidence supporting your case/if any/

   ....................................................................................

6. ሌሎች መገለጽ ያለባቸው ነገሮች ካሉ
   Other related issue you may want to raise

   ....................................................................................

<u>ማሳሰቢያ</u>

- ማንኛውም የግባኝ ወይም መረጃ ለሚመለከተው አካል ብቻ ካልሆነ ለሦስተኛ ወገን አይሰጥም ስሙም አይገለፅም
- Any complaint or information in this regard shall only be submitted to an appropriate authority.